አቢሲንያ ባንክ
Bank of Abyssinia

# የአቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማህበር

## <u>የተሻሻለ ረቂቅ የመመሥረቻ ጽሑፍ</u>

ህዳር 2016 ዓ.ም.
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

## ማውጫ


የዚህ ሠነድ ዓላማ ..... 3
ምዕራፍ አንድ ..... 3
የባንኩ አደረጃጀት፣ ዓላማዎች እና ባለአክሲዮኖች ..... 3
የአክሲዮን ማህበሩ ስም ..... 3
የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መ/ቤት አድራሻ፤ ቅርንጫፎች እና ተቀጥላ ማህበራት ..... 3
የአክሲዮን ማህበሩ የንግድ ዓላማዎችና የሥራ መስክ ..... 4
ምዕራፍ ሁለት ..... 5
የአክሲዮን ካፒታል፣ ከአክሲዮን የሚመነጩ የባለአክሲዮኖች መብቶችና ግዴታዎች ..... 5
የአክሲዮን ማህበሩ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ..... 5
የአክሲዮን ይዞታ ገደብ ..... 6
የአክሲዮኖች ዓይነትና መደብ ..... 6
የባለአክሲዮኖች ስም፤ አድራሻ፤ ዜግነት፤ የፈረሙትን የአክሲዮን ብዛትና የተከፈለውን የገንዘብ መጠን ..... 6
የአክሲዮኖች አከፋፈልና ቀሪ ዋጋቸው ላልተከፈለ አክሲዮኖች ስለሚኖር ኃላፊነት ..... 6
ከአክሲዮን ይዞታ የሚመነጩ የባለአክሲዮኖች መብቶችና ግዴታዎች ..... 7
የአክሲዮን የጋራ ባለቤቶች መብትና ኃላፊነት ..... 7
በመያዣ ወይም በአላባ ስለሚሰጡ አክሲዮኖች ..... 7
የባለአክሲዮኖች መዝገብ ..... 8
አክሲዮኖችን ለሌላ ወገን ስለማስተላለፍ ..... 8
ምዕራፍ ሦስት ..... 9
የአክሲዮን ማህበሩ የሥራ አመራር አካላት እና ሥልጣን ..... 9
የአክሲዮን ማህበሩ የሥራ አመራር አካላት ..... 9
የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ..... 9
የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር ..... 10
የጠቅላላ ጉባዔዎች የጥሪ ማስታወቂያ እና በባለአክሲዮን መዝገብ ስለመጻፍ ..... 11
ውክልና ..... 11
የጥቅም ግጭት ..... 11
መደበኛና አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔዎች ለማካሄድ ስለሚያስፈልገው ምልዓተ-ጉባዔ እና ውሳኔ የሚተላለፍበት ድምጽ ..... 12
የጠቅላላ ጉባኤ ቃለ ጉባዔዎች ..... 13
የዳይሬክተሮች ቦርድ መሰየም እና የሥራ ዘመን ..... 13
የቦርድ አባላት ቁጥር ..... 14
ለማህበሩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች መዝገብ ..... 14

የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣንና ተግባር ..... 14
የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ፣የስብሰባ ቦታ፣አጠራር እና የአሰራር ደንብ ..... 15
የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ ..... 16
ዳይሬክተሮችን ስለመተካት ..... 16
አክሲዮኖችን በዋስትና ስለማስቀመጥ ..... 17
የዋና ስራ አስፈፃሚ እና ምክትል ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚዎች ..... 17
የዋና ሥራ አስፈፃሚ ሥልጣንና ተግባር ..... 17
የውጭ አዲተሮች ስያሜ፤ ኃላፊነትና ተግባር ..... 19
የማህበሩ ጸሐፊ ሹመት፤ ሥልጣንና ተግባር ..... 19
ምዕራፍ አራት ..... 20
ስለባንኩ ሂሳብ አያያዝና ተዛማጅ ተግባራት ..... 20
ጠቅላላ ድንጋጌዎች ..... 20
የፋይናንስ መዝገቦችና መረጃዎች ..... 20
የማህበሩ የሂሳብ ዓመትና ሪፖርት ..... 20
የሂሳብ ሠነዶችን እና ሪፖርቶችን ስለመስጠት ..... 20
በቸልተኝነት ወይም እምነት ማጉደል ምክንያት ለሚደርሱ ኪሣራዎች የሚሸፈኑባቸው መጠባበቂያዎች ..... 21
ሌሎች የመጠባበቂያ ሂሳቦች ..... 21
የትርፍ ድርሻ አመዳደብና አከፋፈል ..... 22
ካፒታል በሚቀነስበት ጊዜ የሚደረግ የትርፍ ክፍፍል ዕገዳ ..... 22
ስለምዝገባና ሪፖርቶችን ይፋ ስለማድረግ ..... 22
ምዕራፍ አምስት ..... 23
ስለባንኩ መፍረስ እና ሂሳብ ስለማጣራት ..... 23
የአክሲዮን ማህበሩን ለማፍረስ የሚያበቁ ምክንያቶች እና አግባብነት ያላቸው ሥነ-ሥርዓቶች ..... 23
ምዕራፍ ስድስት ..... 23
ሌሎች ድንጋጌዎች ..... 23
አክሲዮን ማህበሩ በሥራ የሚቆይበት ጊዜ ..... 23
በከፊል የተሻሩ ሠነዶች ..... 24
ልዩ ልዩ ጉዳዮች ..... 24

# የአቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማህበር
# የተሻሻለ የመመሥረቻ ጽሑፍ

## አንቀጽ አንድ
## የዚህ ሠነድ ዓላማ

አቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማህበር (ከዚህ በኋላ አክሲዮን ማህበር ወይም ባንኩ እየተባለ ይጠቀሳል) በ1952 ዓ.ም የወጣው የንግድ ሕግ በሚደነግገው መሠረት በቁጥር 359113 በ14/5/1988ዓ.ም የተመዘገቡ የመመሥረቻ ጽሑፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ እንዲኖሩት ሆኖ በ1987ዓ.ም. ተመሥርቷል።

በ2013 ዓ.ም. የወጣው የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ (ከዚህ በኋላ የንግድ ሕጉ ተብሎ ይጠቀሳል) የመተዳደሪያ ደንብ ተብሎ ይታወቅ የነበረውን ሠነድ በግልጽ ዕውቅና ያልሰጠው እና በ1952 ዓ.ም. የወጣው የንግድ ሕግ ላይ በመተዳደሪያ ደንብ ላይ ይወሰናሉ የሚባሉ ጉዳዮችን በመመሥረቻ ጽሑፍ ላይ ይወሰናሉ በማለቱ ባንኩ ያለውን የመተዳደሪያ ደንብ ከባንኩ መመሥረቻ ጽሑፍ ጋር በማዋሃድ እና የንግድ ህጉ ካመጣቸው ሌሎች ለውጦች ጋር በማስማማት እና ነባራዊ ለውጦችን በመውሰድ የባንኩን መመሥረቻ ጽሑፍ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል

በመሆኑም፣የባንኩ የባለአክሲዮኖች 14ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ይህን የተሻሻለ የመመሥረቻ ጽሑፍ አጽድቋል፡፡

ይህ ሰነድ "**የአቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማህበር የተሻሻለ መመሥረቻ ጽሑፍ**" ተብሎ ይጠራል፡፡

*(በዚህ ሠነድ በነጠላ ቁጥር የተጠቀሰው አግባብነት ሲኖረው ለብዙም ያገለግላል፡፡ በወንድ ፆታ የተጠሰው አግባብነት ሲኖረው ለሴት ፆታም ያገለግላል፡፡)*

## ምዕራፍ አንድ
## የባንኩ አደረጃጀት፣ ዓላማዎች እና ባለአክሲዮኖች

## አንቀጽ ሁለት
## የአክሲዮን ማህበሩ ስም

የአክሲዮን ማህበሩ "**የአቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማህበር**" በመባል ይታወቃል፡፡

## አንቀጽ ሦስት
## የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መ/ቤት አድራሻ፤ ቅርንጫፎች እና ተቀጥላ ማህበራት

3.1 የአቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ዋና መ/ቤት አድራሻው ኢትዮጵያ፣ አዲስ አበባ ከተማ፣ ቂርቆስ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 07፤ የመልዕክት ሣጥን ቁጥር 12947 ሲሆን አድራሻው እንደ አስፈላጊነቱ ሊቀየር ይችላል፡፡

3.2 አቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማህበር በኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፎችና ንዑስ ቅርጫፎች ያሉት ሲሆን፤ በባንኩ ማኔጅመንት ውሳኔ መሠረት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና ተገቢውን ፈቃድ ከሚመለከተው አካል ሲያገኝ በኢትዮጵያ ተጨማሪ ቅርንጫፎችና ንዑስ ቅርጫፎች እንዲሁም ከኢትዮጵያ ውጭ ቅርንጫፎች እንዲሁም ተቀጥላ ማህበራት (Subsidiaries) ሊከፍት ይችላል፡፡

## አንቀጽ አራት

## የአክሲዮን ማህበሩ የንግድ ዓላማዎችና የሥራ መስክ

የአክሲዮን ማህበሩ የንግድ ዓላማዎችና የሥራ መስኮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

4.1 ልዩ ልዩ ተቀማጭ የአደራ ገንዘቦችን በማሰባሰብ፣ አስፈላጊና የውጤታማ ለሆኑ የኢኮኖሚ ዘርፍ ሥራዎች ያውላል፡፡

4.2 የውጭ ምንዛሪን መግዛት፣ መሸጥና መያዝ፣ የውጭ ምንዛሪ የልውውጥ ሥራ እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ ሥራንና ሌሎች ከውጭ ምንዛሪ ጋር የተያያዙ ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

4.3 የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎቶችን መስጠት እንዲሁም ከባንኩ አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር ሆኖ ማገልገል፣ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር አገልግሎት መስጠት፤

4.4 ከወለድ ነፃ ባንክ አገልግሎትና ሌሎች በየጊዜው የሚፈቀዱ የባንክ ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

4.5 ሲጠየቁ የሚከፈሉ የቁጠባ ሂሳቦችን እና ሌሎች ለተወሰነ ጊዜ በአደራ የሚቀመጡ ሂሳቦችን መቀበል፡፡

4.6 በባንኩና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መካከል በሚደረግ ዝርዝር ስምምነት መሠረት ከመንግሥት ተቀማጭ ገንዘብ መቀበል፡፡

4.7 የተለያዩ ብድሮችንና የቅድሚያ ብድሮችን መፍቀድ፤ ከተቀመጠው ገንዘብ በላይ የሚደረግ ወጭን (ኦቨርድራፍት) መፍቀድና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን መስጠት፡፡

4.8 ለግል ነጋዴዎች እና በቅይጥ የንግድ ሥራ ድርጅቶች (ኢንተርፕራይዝ) ውስጥ ለሚገኙ የግሉ ዘርፍ የገንዘብ ዋስትና ሠነዶችን ለሽያጭ ማቅረብ፡፡

4.9 የብድር፣ የቅድሚያ ክፍያ፣ የመልካም ሥራ አፈፃፀምና የመሳሰሉትን ዋስትናዎች መስጠት፤

4.10 የኢትዮጵያ መንግሥት የሚያወጣቸውን የሚተላለፉ የንግድ ሠነዶች፤ የሚተላለፉ የገንዘብ ዋስትና ሠነዶች (ኔጎሽየብል ሴኪዩሪቲስ)፤ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት፤ ቦታና መሬት እና ሌሎች በመያዣነት የሚሰጡ ንብረቶች፤ ወይም ባንኩ ለሰጣቸው ብድሮች፤ ቅድመ ብድሮች፤ ወይም ኦቨርድራፍቶች ዋስትና/በመያዣነት የተሰጡ ሆነው፤ በስምምነቱ መሠረት ዕዳው በወቅቱ ተከፍሎ ለባለንብረቱ ያልተመለሱትን ሁሉ መያዝ፤ መግዛት እና መሸጥ፡፡

4.11 የዋስትና ሠነዶችን፤ ዕንቁዎችን፤ የከበሩ ድንጋዮችን፤ ሌሎች ዋጋ ያላቸው ነገሮችን ተቀብሎ በአደራ በብረት ካዝናዎች ማስቀመጥ፡፡

4.12 የአክሲዮኖችን፤ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በገንዘብ የሚለወጡ ሠነዶችን እና የግዴታ ሠነዶችን ለማውጣት መደራደር፤ ዋስትና መስጠት እና ማስተዳደር፡፡

4.13 በራሱ ስምና በራሱ ገንዘብ፤ አዋጭ በሆኑ የንግድ ድርጅቶች ውስጥ አክሲዮኖቹን መግዛት፤ እንደ አስፈላጊነቱ አክሲዮኖች መሸጥ፡፡

4.14 ለደንበኞቹ የወኪልነት አገልግሎት መስጠት እና በዚህም ሚናው የገንዘብ እና የዋስትና ሠነዶች ግዢና ሽያጭ ሥራዎችን ማከናወን፡፡

4.15 በዋስትና ወይም ካለዋስትና የዋስትና ወይም የተያዥነት ውሎችን መፈራረም፡፡

4.16 ሥራውን ለማከናወን አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ ለመኖሪያና ለንግድ ሥራ የሚሆኑ ቤቶችን መግዛት፤ ማስተዳደር እና መሸጥ፡፡

4.17 ሥራውን ለማካሄድ ገንዘብ መበደር፤ ለተበደረውም ገንዘብ ንብረቶቹን በዋስትና ለማስያዝ ለአበዳሪዎቹ ግዴታ መግባት፤ ወይም ለአበዳሪዎቹ ማስተላለፍ፡፡

4.18 የሚተላለፉ የምንዛሪ ወረቀቶችን፤ የክፍያ ትዕዛዞችንና የተሰፉ ሠነዶችን በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም ከኢትዮጵያ ውጭ ማውጣት፣ መቀበል፣ መቀነስ መግዛት እና መሸጥ፡፡

4.19 ገቢ ከተደረገው የባንኩ ዋና ገንዘብና ከጠቅላላው መጠባበቂያ ሂሳብ ድምር እስካልበለጠ ድረስ በግል ነጋዴዎች በሚካሄዱ የንግድ ድርጅቶች ውስጥ ኤኩቲ ተሳትፎ ማድረግ፡፡

4.20 የኢትዮጵያ መንግሥት የሚያወጣቸውን የሚተላለፉ የንግድ ሠነዶች፣ የገንዘብ ዋስትና ሠነዶች /ኔጎሼብል ሴኩሪቲስ/፣ መያዝ፣ መግዛት እና መሸጥ፤

4.21 በካፒታል ገበያ ውስጥ አክሲዮኖችን እና ሌሎች ማናቸውንም የፋይናንስ ሠነዶች ወይም አገልግሎቶች መግዛት፣ መሸጥ ወይም መሳተፍ እና ሕግ የሚፈቅደውን ማናቸውንም አገልግሎቶች መስጠት፤

4.22 ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ቅድሚያ በሚሰጥ ፈቃድ መሠረት፣ ስለማናቸውም ንብረት አመዳደብና ክፍፍል አንድ በሕግ የተሾመ አስፈፃሚ ባለአደራ ወይም ባንክ የሚያከናውናቸውን መደበኛ ተግባራት ማከናወን፤

4.23 ደንበኞችን በመወከል የኢንቨስትመንት ፈንዶችን ማስተዳደር፤

4.24 ከባንኩ አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ ለደንበኞች የማማከር አገልግሎት መስጠት፤

4.25 ለአስተማማኝ የባንክ ሥራ ጠቃሚ በሆኑና ከዚህ በላይ በተለይ ባልተዘረዘሩ ማናቸውም በሕግ የሚፈቀዱ ከላይ ከተጠቀሱት ተግባራት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ተመሳሳይ ወይም ተዛማጅነት ያላቸውንና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ ሌሎችንም የባንኩን ዓላማዎች የሚያራምዱ ሁሉም ዓይነት የንግድ ሥራዎች ሁሉ ያከናውናል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## የአክሲዮን ካፒታል፣ ከአክሲዮን የሚመነጩ የባለአክሲዮኖች መብቶችና ግዴታዎች

### አንቀጽ አምስት

### የአክሲዮን ማህበሩ ዋና ገንዘብ (ካፒታል)

5.1 የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ ካፒታል ብር-------------------- (-------------------------ብር) ነው፡፡

5.2 ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የተፈረመ ካፒታል እያንዳንዳቸው ብር 1,000.00 (አንድ ሺህ ብር) ዋጋ ባላቸው -------- (-------------------------) ተራና የተመዘገቡ አክሲዮኖች የተከፋፈለ ነው፡፡

5.3 ከተፈረመው ካፒታል ውስጥ ብር-------------------- (----------------- ብር) በጥሬ ገንዘብ ተከፍሏል፡፡

## አንቀጽ ስድስት

## የአክሲዮን ይዞታ ገደብ

6.1 አንድ ሰው ሊገዛ የሚችለው አነስተኛ የአክሲዮን ብዛት ሁለት መቶ ሃምሳ አክሲዮን ወይም ብር 250,000.00 (ሁለት መቶ ሃምሳ ሺ ብር) ነው፡፡ ይህ የቁጥር ገደብ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ፣ በውርስ፣ በስጦታ፣ ለባንኩ ሠራተኞች ወይም ለነባር ባለአክሲዮኖች የሚደረግ ዝውውርን አይመለከትም፡፡

6.2 ማንኛውም ባለአክሲዮን ከተፈረመው ካፒታል ውስጥ ሕግ የሚፈቅደውን ሁኔታና መጠን ያህል መያዝ ይችላል፡፡

## አንቀጽ ሰባት

## የአክሲዮኖች ዓይነትና መደብ

የአክሲዮን ማህበሩ አክሲዮኖች እኩል ዋጋ ያላቸው ሙሉ ለሙሉ በጥሬ ገንዘብ የሚከፈሉ አንድ ዓይነትና እኩል፤ ልዩ መብት የማይሰጡ የተመዘገቡና ተራ አክሲዮኖች ናቸው፡፡

## አንቀጽ ስምንት

## የባለአክሲዮኖች ስም፤ አድራሻ፤ ዜግነት፤ የፈረሙትን የአክሲዮን ብዛትና የተከፈለውን የገንዘብ መጠን

ይህ ሰነድ ሲዘጋጅ ያሉ የባንኩ ባለአክሲዮች ስም ዝርዝር፤ አድራሻቸው፤ ዜግነታቸውን፤ የፈረሙት አክሲዮን ብዛትና የከፈሉትን የአክሲዮን ዋጋ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ከዚህ የተሻሻለ የመመሥረቻ ጽሑፍ ጋር አባሪ ሆኗል፡፡

## አንቀጽ ዘጠኝ

## የአክሲዮኖች አከፋፈልና ቀሪ ዋጋቸው ላልተከፈለ አክሲዮኖች ስለሚኖር ኃላፊነት

9.1 የባንኩ ባለአክሲዮኖች አዲስ አክሲዮን ለመግዛት በፈረሙ ጊዜ ቢያንስ ቢያንስ የተፈረሙትን አክሲዮኖች 25% ወዲያውኑ መክፈል አለባቸው፡፡ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔው አዲስ አክሲዮን ግዢ በሚፈፀምበት ጊዜ ወዲያውኑ መከፈል የሚኖርበትን የገንዘብ መጠን ከ25% በመጨመር ሊወስን ይችላል፡፡

9.2 ተፈርሞ ያልተከፈለ ቀሪ የአክሲዮን ዋጋ የሚከፈልበት ጊዜ በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔው የሚወሰን ይሆናል፡፡

9.3 የባንኩ ባለአክሲዮኖች፤ አክሲዮኑ ቀደም ሲል ተላልፎላቸው የነበሩ ሰዎች እንዲሁም አክሲዮኑን ከአክሲዮን ማህበሩ ለመግዛት የፈረሙ ሰዎች በተፈረሙ አክሲዮኖች ላይ ላልተከፈለው ቀሪ ገንዘብ ክፍያ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

9.4 አክሲዮኖቹ የተሰጡት በአላባ ጥቅም እንደሆነ፤ ባለአላባው የአላባው ጊዜ መብት ሲያልቅ የከፈለው ገንዘብ እንዲመለስለት ለመጠየቅ ያለው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ባልተከፈለ የአክሲዮን ገንዘብ ጥሪው መሠረት ቀሪው ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡

9.5 ዋጋቸው ያልተከፈለ አክሲዮኖች ቀሪ ሂሳብ እንዲከፈል ጥሪ ከተሰጠ በኃላ ይህንኑ በተወሰነው ቀን ካልተከፈለ የንግድ ሕግ አንቀጽ 289 ከንዑስ አንቀጽ 3 እስከ 7 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ አሥር

## ከአክሲዮን ይዞታ የሚመነጩ የባለአክሲዮኖች መብቶችና ግዴታዎች

10.1 አግባብ ያላቸው ሕጐችና ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ አክሲዮኖች ለእያንዳንዱ ባለአክሲዮን የሚከተሉትን መብቶች ያሰጣሉ፡፡

10.1.1 በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የመገኘትና የመሳተፍ፣

10.1.2 በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሚጸድቀውን የትርፍ ድርሻ የማግኘት፣

10.1.3 በሕግ መሠረት ድምጽ የመስጠት መብትን የሚያሳጡ ሁኔታዎች ከሌሉ በስተቀር በእያንዳንዱ አክሲዮን አንድ ድምጽ የመስጠት መብት፣

10.1.4 ካፒታል ለመጨመር በጥሬ ገንዘብ የሚሸጥ አዲስ አክሲዮኖች በሚወጡበት ጊዜ እያንዳንዱ ባለአክሲዮን አስቀድሞ በያዛቸው አክሲዮኖች መጠን ልክ አዲስ አክሲዮን የመግዛት የቅድሚያ መብት፡፡

10.1.5 ቃለ-ጉባዔዎችን እና ጠቅላላ ስብሰባዎች ላይ የተገኙ አባላትን ስም ዝርዝር የመመልከት መብት እንዲሁም የሀብትና ዕዳ፤ የትርፍና የኪሣራ ሂሳብ ሚዛን፤ የዳይሬክተሮች ቦርድ እና የኦዲተሮች ሪፖርቶችን ቅጅዎች የመውሰድ መብት፡፡

10.1.6 አክሲዮን ማህበሩ በመክሰር ወይም በሌላ ምክንያት ሥራ በሚያቆምበትና ንብረቱ በሚጣራበት ጊዜ ለካፒታል ባስገባው መዋጮ መጠን ተሰልቶ ከተላለፈው ንብረት ላይ ድርሻውን የማግኘት፤

10.1.7 በዚህ ንዑስ አንቀጽ 10.1.2፣ 10.1.4 እና 10.1.6 የተመለከቱትን መብቶች የሚያስገኙት ዋጋቸው በሙሉ በተከፈሉ አክሲዮኖች ብቻ ናቸው፡፡

10.2 የባለአክሲዮኖች ግዴታዎች፤ በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍና አግባብነት ባላቸው ሕጐችና ድንጋጌዎች መሠረት የሚመሩ ሆኖ፤ ባለአክሲዮኖች ለማህበሩ ዕዳ ወይም ግዴታ ተጠያቂ የሚሆኑት በስማቸው በያዟቸው አክሲዮኖች ዋጋ መጠን ልክ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ አሥራ አንድ

## የአክሲዮን የጋራ ባለቤቶች መብትና ኃላፊነት

11.1 ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች አክሲዮን በጋራ መግዛት ይችላሉ፡፡ እንደዚህ በሚሆንበት ጊዜ የባለአክሲዮንነት መብታቸውን የሚጠቀሙት የጋራ ወኪል በመሾም ነው፡፡

11.2 የጋራ ወኪል ባልሾሙ ጊዜ ማህበሩ ለአንዱ ባለአክሲዮን የጋራ ባለቤት የሚሰጠው ማስታወቂያ ወይም መግለጫ ለቀሪዎቹ የአክሲዮኑ የጋራ ባለቤቶችም ጭምር እንደተሰጠ ይቆጠራል፡፡

11.3 የአክሲዮን የጋራ ባለቤቶች ከባለአክሲዮንነት ለሚመነጩ ኃላፊነቶች በአንድነትና በተናጠል ተጠያቂ ናቸው፡፡

## አንቀጽ አሥራ ሁለት

## በመያዣ ወይም በአላባ ስለሚሰጡ አክሲዮኖች

12.1 የተለየ ስምምነት በሌለ ጊዜ፤ አክሲዮኖቹ በመያዣ ወይም በአላባ ጥቅም የተሰጡት እንደሆነ፤ በማህበሩ ጉባዔዎች ድምፅ የመስጠት መብት የሚኖረው አክሲዮኑን በመያዣ የያዘው ወይም የአላባ ጥቅም ያለው ሰው ነው፡፡

12.2 ለነባር ባለአክሲዮኖች አዲስ አክሲዮን ለመግዛት በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ የተቀመጠውን የቅድሚያ የመግዛት መብት የባለአክሲዮኑ ሆኖ ይቀጥላል፡፡

12.3 በመያዣ ለተሰጠ አክሲዮን የሚከፈል ቀሪ ገንዘብ መክፈል ያለበት ባለአክሲዮኑ ነው፡፡

## አንቀጽ አሥራ ሦስት

## የባለአክሲዮኖች መዝገብ

13.1 አክሲዮን ማህበሩ የባለአክሲዮኖችን መዝገብ መያዝ አለበት፡፡ መዝገቡ በአክሲዮን ማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት መያዝ ያለበት ሲሆን፣ በወረቀት ወይም ለረዥም ዘመን በሚቆይ የኤሌክትሮኒክ ዘዴ መያዝ ይችላል፡፡

13.2 መዝገቡ የባለአክሲዮኖችን ስም፣ አድራሻ፣ ዜግነት፣ የአክሲዮኖች ብዛትና መለያ ቁጥር፣ የተከፈለውን ገንዘብ መጠንና ባለአክሲዮኖቹ የተመዘገቡበትን ቀን መያዝ አለበት፡፡

13.3 መዝገቡ ማንኛውም ባለአክሲዮን እና ማንኛውም በሕግ የተፈቀደለት ሰው ሊመለከተው እንዲችል ሆኖ በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት ለረጅም ጊዜ በሚቆይ መልኩ በወረቀት ሠነድ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ተይዞ በመደበኛ የሥራ ሰዓታት ሁሉ ክፍት ሆኖ ይቀመጣል።

13.4 መዝገቡን ባለአክሲዮኖች እና ማንኛውም በሕግ የተፈቀደለት ሰው የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጽም የመዝገቡን ግልባጭ ወይም በአጭር የተውጣጣ ጽሑፍ እንዲሰጠው አክሲዮን ማህበሩን መጠየቅ ይችላል፡፡

## አንቀጽ አሥራ አራት

## አክሲዮኖችን ለሌላ ወገን ስለማስተላለፍ

14.1 አክሲዮኖች በአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ያለምንም ገደብ ይተላለፋሉ፡፡ በዚህ የመመሥረቻ ጽሑፍ አንቀፅ 6 እና አግባብነት ያላቸው ገደቦች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

14.2 አክሲዮኖች ለሌላ ወገን በሚተላለፉበት ጊዜ ይኸው ሁኔታ በባለአክሲዮኖች መዝገብ ላይ መጻፍ ያለበት ሲሆን በባለአክሲዮኖች መዝገብ ላይ ካልተጻፈ በስተቀር የአክሲዮን መብት ለተላለፈለት ሰው የተሟላ ሆኖ አይቆጠርም፡፡ የአክሲዮን ዝውውሩም ዋጋ አይኖረውም፡፡

14.3 አክሲዮኖች በጋራ ከያዙ ባለአክሲዮኖች መካከል አንዱ ቢሞት የሟች የአክሲዮን ድርሻ ላይ መብት የሚኖራቸው በሕይወት የሚገኘው (የሚገኙት) የሟቹ ወራሽ /ወራሾች/ ይሆናል፡፡

14.4 አክሲዮኖች በጋራ የያዙ ባለአክሲዮኖች የባለአክሲዮንነት መብታቸውን መጠቀም የሚችሉት የጋራ ወኪል በመሾም ሲሆን ከባለአክሲዮንነት ለሚመነጩ ኃላፊነቶች በአንድነትና በተናጠል ተጠያቂዎች ናቸው፡፡

14.5 ማንኛውንም ሰው ተደማጭነት ያለው ባለአክሲዮን ሊያደርግ የሚችል የአክሲዮን ዝውውር በአክሲዮን መዝገብ ከመመዝገቡ በፊት በብሔራዊ ባንክ መጽደቅ አለበት፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የአክሲዮን ማህበሩ የሥራ አመራር አካላት እና ሥልጣን

### አንቀጽ አሥራ አምስት
### የአክሲዮን ማህበሩ የሥራ አመራር አካላት

የአክሲዮን ማህበሩ የሥራ አመራር አካላት የሚከተሉት ናቸው፡፡

15.1 የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ

15.2 የዳይሬክተሮች ቦርድ

15.3 ዋና ሥራ አስፈፃሚ

15.4 ኦዲተሮች

15.5 የማህበሩ ፀሐፊ

### አንቀጽ አሥራ ስድስት

### የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ

16.1 የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ መደበኛ ወይም አስቸኳይ ናቸው፡፡

16.2 መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ኦዲተሮች በሚያደርጉት ጥሪ መሠረት የበጀት ዓመቱ በተዘጋ በስድስት ወራት ውስጥ በዓመት አንድ ጊዜ መደረግ አለበት፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔዎች ሊደረጉ ይችላሉ፡፡

16.3 የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ የሚያደርጉት እንደነገሩ ሁኔታ የዳይሬክተሮች ቦርድ፣ ኦዲተሮች፣ ሒሳብ አጣሪዎች ወይም ፍርድ ቤት ናቸው።

16.4 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 16.2 ሥር የተመለከተው ቢኖርም የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም አግባብ ያለው ሌላ የመንግሥት አካል ጉዳዩ አንገብጋቢ ሆኖ ሲያገኘው እና በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 16.2 መሠረት ስብሰባ መጥራት የማይቻል ወይም ረጅም ጊዜ የሚወስድ ከሆነ በጉዳዩ ያገባኛል በሚል ማንኛውም ሰው ጥያቄ ወይም በራሱ ተነሳሽነት ጉባዔ ሊጠራ ይችላል፣ ሆኖም ጉባዔ እንዲጠራ ጥያቄ የቀረበው የባንኩን ዋና ገንዘብ አሥር በመቶ ወይም ከዚያ በላይ በሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ከሆነ የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም አግባብ ያለው ሌላ የመንግሥት አካል ጉባዔ የመጥራት ግዴታ አለበት።

16.5 ከባንኩ ዋና ገንዘብ ቢያንስ አምስት በመቶ ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች የባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት በሚገኝበት ቦታ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ጥያቄ ሲያቀርቡና ፍርድ ቤቱ ጥያቄው ተገቢ ነው ብሎ ሲያምን ጠቅላላ ጉባዔ እንዲሰበሰብ ጥሪ የሚያደርግና አጀንዳ የሚያዘጋጅ ተወካይ ሊሰይም ይችላል፡፡

16.6 በጠቅላላ ጉባዔ ላይ ባለአክሲዮኖች በአካል በመገኘት ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ወይም ሁሉም ባለአክሲዮኖች የተስማሙ እንደሆነ ስብሰባ ማድረግ ሳያስፈልግ ለውሳኔ በቀረበ ጉዳይ ላይ ሃሳባቸውን በጽሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በመግለጽ ውሳኔ ማስተላለፍ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ አሥራ ሰባት

## የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር

17.1 የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የአክሲዮን ማህበሩ የሥራ አመራር የበላይ አካል ነው፡፡

17.2 የባለአክሲዮኖች የተለያዩ ዓይነት ጠቅላላ ጉባዔዎች በንግድ ሕግና በዚህ የአክሲዮን ማህበሩ የመመሥረቻ ጽሑፍ በተወሰነው መሠረት ይካሄዳል፡፡

17.3 በንግድ ሕግና አግባብነት ባላቸው የባንክ ሥራ ሕጐች ውስጥ የተደነገገው የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጠቃላይ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው እንደአስፈላጊነቱ የሚከተሉት ሥልጣኖች ይኖሩታል፡-

17.3.1 የቦርድ ዳይሬክተሮችን ይሰይማል፣ ይሽራል፣ ክፍያቸውንም ይወስናል፣

17.3.2 የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ፤ አባላትን ይሾማል፤ ይሽራል፤ ክፍያቸውንም ይወስናል፡፡

17.3.3 የባንኩን የሀብትና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ፤ የትርፍና ኪሣራ ሂሳብ እንዲሁም የዳይሬክተሮች ቦርድን ሪፖርት፣ የኦዲተሮችን ሪፖርት አድምጦ የማሻሻል ወይም የማጽደቅ፤ ወይም ያለመቀበል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በትርፍ አመዳደብ እና አከፋፈል እንዲሁም በአጠቃላይ ያለፈውን የሂሳብ ዓመት ማጠቃለያ የተመለከቱ የሂሳብ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ያስተላልፋል፤

17.3.4 የባንኩን ኦዲተሮች ይሰይማል፣ ይሽራል፤ የሥራ ጊዜያቸውንና የሚከፈላቸውንም ክፍያ ይወስናል፣

17.3.5 በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ ወይም አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲወስንባቸው ተለይተው ከተቀመጡት ውጭ ያሉ ጉዳዮች ላይ ጠቅላላ ጉባዔው ይወስናል፡፡

17.4 አግባብነት ባላቸው ሕጐች እና በንግድ ሕግ ውስጥ የተደነገገው የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ አጠቃላይ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔው እንደአስፈላጊነቱ የሚከተሉት ሥልጣኖች ይኖሩታል፣

17.4.1 በመመሥረቻ ጽሑፉ ላይ ማሻሻያዎችን ያደርጋል፣

17.4.2 የባንኩን ዓላማዎች ያሻሽላል፣

17.4.3 የባንኩን ዋና ካፒታል ይቀንሳል ወይም ይጨምራል፣

17.4.4 ባንኩ እንዲፈርስና ሂሳቡም እንዲጣራ ይወስናል፣

17.4.5 ባንኩ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ሌላ ባንክ ወይንም የፋይናንስ ተቋም ወይንም ድርጅት እንዲጠቃለል፣ ከሌላ ባንክ ወይንም የፋይናንስ ተቋም ወይንም ድርጅት ጋር እንዲዋሀድ ወይም ባንኩ እንዲከፋፈል ሊወስን ይችላል፡፡

17.5 ለጉባዔው ዓይነትና የአጀንዳ ነጥቡ እና በሕግ የሚጠየቀው ምልዓተ ጉባዔ እንደተጠበቀ ሆኖ በጠቅላላ ጉባዔ የተላለፉ ውሳኔዎች በሁሉም ባለአክሲዮኖች፣ በባለአክሲዮኖች በሙሉ በመወከል በስብሰባ ባልተገኙት፣ በሃሳብ በተለዩት፤ በውሳኔው ባልተስማሙ፣ ድምጽ ባልሰጡ ወይም ለመስጠት በማይችሉ ባለአክሲዮኖች ላይ ጭምር ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

17.6 ከላይ በ17.5 የተደነገገው ቢኖርም ባለአክሲዮኑ ራሱ ካልተስማማ በስተቀር ባለአክሲዮኑ አባል በመሆኑ ምክንያት ሊያገኝ የሚገባውን መሠረታዊ መብት ጠቅላላ ጉባዔው ሊነፍገው አይችልም፡፡

## አንቀጽ አሥራ ስምንት

## የጠቅላላ ጉባዔዎች የጥሪ ማስታወቂያ እና በባለአክሲዮን መዝገብ ስለመጻፍ

18.1 ጠቅላላ ጉባዔ መጥራት በሚያስፈልግበት ጊዜ ከስብሰባው ዕለት 24 (ሃያ አራት) ቀናት አስቀድሞ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ የስብሰባው ጥሪ መተላለፍ አለበት፡፡ ወይንም ስብሰባው በባንኩ ወጪ በተመዘገበ ደብዳቤ ወይም የኢሜይል አድራሻ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሊጠራ ይችላል።

18.2 የጥሪ ማስታወቂያው በፖስታ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ለእያንዳንዱ ባለአክሲዮን የሚተላለፍ ቢሆንም ስብሰባውን በሚጠራው አካል ውሳኔ መሠረት ጥሪው በተጨማሪ በጋዜጣ ሊደረግ ይችላል።

18.3 ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 18.1 እና 18.2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሌላ ማስታወቂያ ለባለአክሲዮኑ የሚተላለፍለት በአስመዘገበው አድራሻ መሠረት እንደአመቺነቱ በመልዕክተኛ፣ በፖስታ፣ በፋክስ፣ በኢሜል፣ በስልክ የጽሑፍ መልዕክት ወይም በሬዲዮ ወይም በጋዜጣ ሊሆን ይችላል፡፡

18.4 ማንኛውም የአክሲዮን ባለሀብት በባለአክሲዮኖች መዝገብ ውስጥ መጻፍ የሚችለው ጠቅላላ ጉባዔው ከሚደረግበት ቀን 10 የሥራ ቀናት አስቀድሞ ነው። ይህ ሁኔታም የጥሪ ማስታወቂያው ላይ ይገለጻል፡፡

## አንቀጽ አሥራ ዘጠኝ

## ውክልና

19.1 የውክልና ሠነዶች ጠቅላላ ጉባዔ ከሚደረግበት ዕለት በፊት ሦስት ቀን አስቀድሞ ለባንኩ ዋና መ/ቤት መቅረብ አለባቸው፡፡

19.2 በጉባዔው ላይ ለመገኘት የሚያስችል የውክልና ይዘት፣ ተሞልተው የሚላኩበት የጊዜ ገደብና ቦታው በዳይሬክተሮች ቦርድ ተወስኖ በጥሪው ማስታወቂያ ላይ መገለጽ አለባቸው፡፡

19.3 አንድ የባንኩ ባለአክሲዮን በሌላ ሰው ወይም የባንኩ ባለአክሲዮን በሆነ ሰው ሊወከል ይችላል፡፡

## አንቀጽ ሃያ

## የጥቅም ግጭት

20.1 በራሱ ስም ወይም ሌላ ሦስተኛ ወገንን ወክሎ በጉባዔ ላይ የሚገኝ ተሳታፊ ከባንኩ ጥቅሞች ጋር የሚጋጭ ጥቅም ያለው ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ተሳታፊው በቀረበው ጉዳይ ላይ ድምጽ የመስጠት መብት አይኖረውም፡፡

20.2 ዳይሬክተሮች የራሳቸውን ኃላፊነትና ግዴታ በሚመለከት ውሳኔ ላይ ድምጽ የመስጠት መብት አይኖራቸውም፡፡

20.3 ምልዓተ-ጉባዔ በሚሰላበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ መሠረት ድምፅ የመስጠት መብት የተነፈጋቸው አክሲዮኖች ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡

## አንቀጽ ሃያ አንድ

## መደበኛና አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔዎች ለማካሄድ ስለሚያስፈልገው ምልዓተ-ጉባዔ እና ውሳኔ የሚተላለፍበት ድምጽ

21.1 መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ፡-

21.1.1 በመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የመጀመሪያ ጥሪ፣ ድምጽ የመስጠት መብት ከሚሰጡ የባንክ አክሲዮኖች ቢያንስ አንድ አራተኛ (1/4) የያዙ ባለአክሲዮኖች ራሳቸው ወይም እንደራሴዎቻቸው መገኘት አለባቸው፡፡

21.1.2 በሁለተኛው ጥሪ የተወከሉት ድምጽ የመስጠት መብት የሚሰጡት አክሲዮኖች ቁጥር የትኛውንም ያህል ቢሆን፣ ጉባዔው ስብሰባውን ለማካሄድና ውሳኔ ለማስተላለፍ ይችላል፡፡

21.1.3 ጉባዔው ላይ ድምጸ ተአቅቦዎችን እና ባዶ ድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ከግምት ውጭ በማድረግ በመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች የሚጸድቁት በድምጽ ብልጫ ይሆናል፡፡

21.2 አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ፡-

21.2.1 የባንኩ ዜግነት እንዲለወጥ የሚያደርጉ ወይም በነባር አክሲዮኖች ላይ የተጻፈውን ዋጋ በመጨመር የባንኩን ካፒታል ከፍ እንዲደረግ የሚጠይቁ ውሳኔዎች ሁሉ ዋጋ ሊኖራቸው የሚችለው ድምጽ ለመስጠት መብት ያላቸው አክሲዮኖች የያዙ ባለአክሲዮኖች በአስቸኳይ ጉባዔው ላይ ተገኝተው ወይም ተወክለው በሙሉ ድምፅ ሲስማሙበት ብቻ ይሆናል፡፡

21.2.2 በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 21.2.1 የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም አስቸኳይ ጉባዔ ላይ ውሳኔዎች በሁለት ሶስተኛ (2/3ኛ) አብላጫ ድምጽ የሚጸድቁ ሆኖ በሚከተለው መሠረት አፈጻጸሙ ይወሰናል፡፡ ለድምጽ ብልጫው አቆጣጠር ስሌት ድምጽ ያልሰጡም ሆነ ድምጽ ያልተጻፈባቸው የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ግምት ውስጥ አይገቡም፡፡

21.2.2.1 በመጀመሪያ ጉባዔ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ከአንድ ሶስተኛ (1/3) ያላነሱትን የያዙ ባለአክሲዮኖች ሲገኙ፣ ወይም ሲወከሉ፣

21.2.2.2 በሁለተኛው ጉባዔ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው የተፈረሙ አክሲዮኖች ከአንድ አራተኛ (1/4) ያላነሱ ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸው አክሲዮኖችን የያዙ ባለአክሲዮኖች ሲገኙ ወይም ሲወከሉ፣

21.2.2.3 በሦስተኛው ጉባዔ የተወከሉት ድምጽ የመስጠት መብት የሚሰጡት አክሲዮኖች ቁጥር የትኛውንም ያህል ቢሆን፣ ጉባዔው ስብሰባውን ለማካሄድና ውሳኔ ለማስተላለፍ ይችላል፡፡

21.3 ሕግንና ይህን የመመሥረቻ ጽሑፍን በመተላለፍ በመደበኛም ሆነ በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ በተሰጡ ውሳኔዎች ጥቅሙ የተጎዳ ሰው፣ ውሳኔዎቹ ከተሰጡበት ቀን ጀምሮ በዘጠና ቀናት ውስጥ መቃወሚያ ሊያቀርብባቸው ይችላል፡፡ የአንድ ጉባዔ ውሳኔ እንዲሻር ወይም እንዲሰረዝ የሚቀርበው መቃወሚያ ላይ የንግድ ሕግ አንቀጽ 391 ንዑስ አንቀጽ (2-7) ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ ሃያ ሁለት
## የጠቅላላ ጉባዔ ቃለ ጉባዔዎች

22.1 በጠቅላላ ጉባዔዎች ላይ የሚደረጉ ውይይቶች በቃለ-ጉባዔ መያዝ አለባቸው፡፡ ቃለ-ጉባዔዎች በስብሰባው ላይ በተገኙት ዳይሬክተሮች እና በአክሲዮን ማህበሩ ፀሐፊ ይፈረማሉ፡፡

22.2 ቃለ-ጉባዔ ወደ መዝገብ በትክክል ስለመገልበጡ በአክሲዮን ማህበሩ የቦርድ ሰብሳቢ ወይም በሌሎች ሁለት የቦርድ አባላት መረጋገጥ አለበት፡፡

22.3 የጠቅላላ ጉባዔ ቃለ-ጉባዔዎች በተለይ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ጉዳዮች መያዝ አለባቸው፡፡

22.3.1 የጉባዔውን ጥሪ አደራረግ፤

22.3.2 የስብሰባውን ቦታና ቀን፤

22.3.3 አጀንዳዎቹን፤

22.3.4 በጉባዔው የተገኙ የቦርድ አባላትን ስም፤

22.3.5 በስብሰባው ላይ የተገኙ አክሲዮኖችን ብዛትና የምልዓተ ጉባዔውን ቁጥር፤

22.3.6 ለጉባዔው የቀረቡትን ሠነዶች፤

22.3.7 የውይይቱን አጭር ማጠቃለያ፤

22.3.8 የተሰጡትን ድምጾች ውጤት እና፤

22.3.9 ጉባዔው ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች፤

## አንቀጽ ሃያ ሦስት
## የዳይሬክተሮች ቦርድ መሰየም እና የሥራ ዘመን

23.1 ባንኩ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የዳይሬክተሮች ቦርድ ይመራል፡፡ በቦርድ አባልነት ሊሾሙ የሚችሉት ዳይሬክተሮች ባለአክሲዮኖች የሆኑ ብቻ ናቸው፡፡

23.2 የዳይሬክተሮች የሥራ ዘመን ሦስት(3) ዓመት ነው፡፡ ዳይሬክተሮቹ በየ3 /በየሶስት/ ዓመቱ ይመረጣሉ፡፡

23.3 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያወጣው መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥራ ተከታታይነት እንዲኖረው በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ሲወሰን በየምርጫው ለሁለት ተከታታይ የሥራ-ዘመን ካገለገለ ነባር ዳይሬክተሮች ከጠቅላላ ቦርድ አባላት ውስጥ ቢበዛ 1/3 /አንድ ሦስተኛው/ ለሦስተኛ የሥራ-ዘመን እንደገና መመረጥ ይችላል፡፡ እንደገና የተመረጡት የቦርድ ዳይሬክተሮች ለአንድ የቦርድ የሥራ ዘመን ብቻ ያገለግላሉ፡፡

23.4 በአንቀጽ 23.3 የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ዳይሬክተር ከስድስት ተከታታይ ዓመታት በላይ በባንኩ በዲይሬክተርነት ማገልገል አይችልም። ሆኖም የዳይሬክተሩ አገልግሎት ካበቃ ከ6 (ስድስት) ዓመታት በኃላ እንደገና መመረጥ ይችላል።

23.5 ጠቅላላ ጉባዔው በሕጉ እና በዚህ መመሥረቻ ጹሑፍ በተገለፀው መሠረት ዳይሬክተሮችን በማናቸውም ጊዜ የማሰናበት ሥልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው፣ የ3(ሦስቱ) ዓመት የሥራ

ዘመን ከማለቁ በፊት ከ50% በላይ ዳይሬክተሮች የሥራ ስንብት ሲያቀርቡና አዲስ ምርጫ እንዲካሄድ ጠቅላላ ጉባዔውን ሊጠይቅ ይችላል።

23.6 ዳይሬክተሮቹ ሥራቸውን ሲለቁና አዲስ ለተመረጡት ዳይሬክተሮች ሥራቸውን ማስተላለፍ የሚችሉት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ካገኙ በኋላ ነው፡፡ በዚህ አንቀጽ መሠረት እስከሚተኩ ድረስ ነባር ዳይሬክተሮች ባንኩን የማገልገል ግዴታ አለባቸው፡፡

23.7 ብሔራዊ ባንክ አዲስ የተመረጡ ዳይሬክተሮችን ሹመት በጽሑፍ እስኪያጸድቅ ድረስ የነባር ዳይሬክተሮች የሥራ ዘመን ሳይቋረጥ ይቀጥላል፡፡

23.8 ቦርዱ ከአባላቱ መካከል ሊቀመንበር ይመርጣል፡፡

## አንቀጽ ሃያ አራት

## የቦርድ አባላት ቁጥር

24.1 ባንኩ 9 (ዘጠኝ) የቦርድ አባላት/ዳይሬክተሮች ይኖሩታል፡፡

## አንቀጽ ሃያ አምስት
## ለማህበሩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች መዝገብ

25.1 ባንኩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች መዝገብ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 311 መሠረት ይይዛል፡፡

25.2 ባለአክሲዮኖች እና የመንግሥት መሥሪያ ቤት ተወካዮች መዝገቡን በነጻ ማየት ይችላሉ፤ ባለአክሲዮን ያልሆኑ ሰዎች ለዚሁ የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ በመፈጸም መዝገቡን የማየት መብት አላቸው፡፡

## አንቀጽ ሃያ ስድስት
## የዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣንና ተግባር

26.1 የዳይሬክተሮች ቦርድ አግባብነት ባላቸው ሕጎች፣ በባንኩ መመሥረቻ ጽሑፍ እና በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች የተሰጠ ወይም የሚሰጥ ተግባርና ሥልጣን ይኖረዋል።

26.2 በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ ወይም በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሠረት ለሌላ የባንኩ አካል በሕግ ተለይቶ የተሰጠ ካልሆነ በስተቀር ለባንኩ የተሰጡ ሥልጣኖች ሁሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥልጣኖች ይሆናሉ፡፡

26.3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 26.1 የተጠቀሰው አጠቃላይ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣኖች ይኖሩታል ፡

26.3.1 የአክሲዮን ማህበሩን ሥራ አመራር ይቆጣጠራል፡፡

26.3.2 የአክሲዮን ማህበሩን ዋና የሥራ አስፈፃሚ፣ የውስጥ ኦዲት ኃላፊና የሪስክና ኮምፕሊያንስ ኃላፊን መርጦ ይሾማል፡፡

26.3.3 የዋና ሥራ አስፈፃሚ ምክትል የሆኑ ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚዎች /ሲኒየር ኤክስኪዩቲቭ ኦፊሰሮች/ በዋና ሥራ አስፈፃሚ ተመርጠው ሲቀርቡለት ሹመታቸውን ያጸድቃል፡፡

26.3.4 የአክሲዮን ማህበሩ ጸሐፊ ቅጥርና ስንብት በዋና ሥራ አስፈፃሚ ሲቀርብለት ያጸድቃል፡፡

26.3.5 የአክሲዮን ማህበሩን ስትራቴጂዎችን፣ ፖሊሲዎችን፣ ሲስተሞችንና ዓመታዊ ዕቅድና በጀት በዋና ሥራ አስፈፃሚው ተዘጋጅተው ሲቀርቡለት በአግባቡ ተመልክቶና ከልሶ ያጸድቃል፡፡

26.3.6 የአክሲዮን ማህበሩ ዓላማዎች ግባቸውን እንዲመቱ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

26.3.7 ከኢትዮጵያ ውጪ ስለሚከፈቱ ቅርንጫፎች ውሳኔ ይሰጣል፡፡

26.3.8 በዋና ሥራ አስፈፃሚው የሚቀርቡለትን የኢንቨስትመንትና የቋሚ ንብረት ግዥ ጥያቄዎች ያጸድቃል፡፡

26.3.9 አስፈላጊ መስሎ የሚታየውን ማናቸውንም ምክረ ሃሳቦች ለባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡

26.3.10 አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ተለይተው ለሚታወቁ ጉዳዮች ብቻ የዳይሬክተሮች ቦርድ ለቦርዱ ሰብሳቢ እና/ወይም ለዋና ሥራ አስፈፃሚ የውክልና ሥልጣን ሊሰጥ ይችላል፡፡

26.3.11 የዳይሬክተሮች ቦርድ ከላይ ከተጠቀሱት ስልጣኖች በተጨማሪ የማይንቀሳቀሱ ወይም የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን የመግዛት፣ የመሸጥ እና የመለወጥ ጉዳዮች ላይ መወሰን ሥልጣን አለው፡፡ ቦርዱ ይህን ሥልጣኑን በቃለ-ጉባዔ ለዋና ሥራ አስፈፃሚ ሊያስተላልፍ ይችላል።

26.3.12 የዳይሬክተሮች ቦርድ የባንኩን የማይንቀሳቀሱ ቋሚ ንብረቶች በማስያዝ ከባንኩ ጠቅላላ ካፒታል 25% (ሃያ አምስት በመቶ) ሳይበልጥ ለባንኩ ጥቅም መበደር ይችላል፡፡ ቦርዱ ይህን ሥልጣኑን በቃለ-ጉባዔ ለዋና ሥራ አስፈፃሚ ሊያስተላልፍ ይችላል።

26.3.13 የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊሰበሰቡ የማይችሉ ብድሮችንና ሌሎች ተሰብሳቢ ክፍያዎችን መሠረታዊ የሂሳብ አያያዝ መርሆችን በመከተል ከሂሳብ መዝገብ ላይ ሊሰርዝ ይችላል፡፡ እንዲሁም አገልግሎት መስጠት የማይችሉትን ቋሚ ንብረቶች ማስወገድ ወይም ከመዝገብ ላይ መሰረዝ ይችላል፡፡ ቦርዱ ይህን ሥልጣኑን በቃለ-ጉባዔ ለዋና ሥራ አስፈፃሚ ሊያስተላልፍ ይችላል።

26.3.14 ቦርዱ የባንኩን የአክሲዮኖች ግዢ እና ሽያጭ አገልግሎቶች እና ሌሎች የገንዘብ ሠነዶችን በካፒታል ገበያ ላይ አገልግሎት መስጠትን እንዲሁም በካፒታል ገበያ ላይ ያሉ ሌሎች ተሳትፎዎችን ይወስናል፡፡

26.3.15 አንድ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል በሕጉ፣ በመመሥረቻ ጽሑፍና በጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ የተጣለበትን ኃላፊነት በሕጋዊ መንገድ በሚያከናውንበት ጊዜ ለሚከሰቱ ዕዳዎች በግል ተጠያቂ አይሆንም፡፡ ዳይሬክተሩ በቸልተኝነት፣ እምነት ወይም ኃላፊነቱን በማጉደል ለሠራው ሥራዎች ግን ከኃላፊነት ነጻ አይሆንም፡፡

## <u>አንቀጽ ሃያ ሰባት</u>

## <u>የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ፣ የስብሰባ ቦታ፣ አጠራር እና የአሰራር ደንብ</u>

27.1 የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ እና ም/ሰብሳቢ በዳይሬክተሮች ቦርድ ይመረጣሉ።

27.2 ሰብሳቢው የቦርድ ስብሰባ የመጥራት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ የዳይሬክተሮች ቦርድ በባንኩ ዋና ጽ/ቤት ወይም ሰብሳቢው በሚመርጠው በሌላ ቦታ ቢያንስ በወር 1/አንድ/ ጊዜ ይሰበሰባል፡፡ ከዚህም ሌላ የባንኩ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በሚያስፈልገው መጠን ተጨማሪ ስብሰባዎች ሊያካሄድ ይችላል፡፡

27.3 የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ሰብሳቢው የቦርድ ስብሰባዎችን ሁሉ በሰብሳቢነት ያካሂዳል፡፡ ነገር ግን ሁለቱም በማይኖሩበት ጊዜ በስብሰባው በሚሰየም ማናቸውም የቦርድ አባል/ዳይሬክተር ይመራል፡፡

27.4 የዳይሬክተሮች ቦርድ የባንኩን መመሥረቻ ጽሑፍና የንግድ ሕጉን መሠረት በማድረግ የራሱን የአሠራር ሥነ-ሥርዓት ደንብ ማዘጋጀት ይችላል፡፡

## አንቀጽ ሃያ ስምንት
## የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ

28.1 ከጠቅላላው ዳይሬክተሮች ቁጥር 51% (ሃምሣ አንድ በመቶ) የሚሆኑት በስብሰባው ላይ በራሳቸው ወይም በወኪላቸው ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ካልተገኙ በስተቀር የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ ማሳለፍ አይችልም፡፡ ውሳኔ የሚተላለፈው በድምጽ ብልጫ ነው፡፡ ማንኛውም ዳይሬክተር ወይም ተወካይ ድምጽ የመስጠት መብት ይኖረዋል፡፡ ድምጽ እኩል ለእኩል በሚከፈልበት ጊዜ የቦርዱ ሰብሳቢ የደገፈው ሀሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

28.2 በቦርድ ስብሰባ ለመገኘት የማይችል ዳይሬክተር የሚወከለው በሌላ ዳይሬክተር ብቻ ይሆናል፡፡ አንድ ዳይሬክተር ሊወክል የሚችለው አንድ ሌላ ዳይሬክተር ብቻ ነው፡፡

28.3 የቦርድ ውሳኔዎች በቃለ-ጉባዔ ተይዘው በስብሰባው ላይ በተገኙ ዳይሬክተሮች እና በማህበሩ ጸሐፊ ይፈረማሉ፡፡ ቃለ-ጉባዔዎች በመዝገብ ይቀመጣሉ፡፡

28.4 ከቦርዱ ጠቅላላ አባላት ውስጥ ቢያንስ አንድ ሦስተኛው በስብሰባው ላይ በአካል ካልተገኙ በስተቀር በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በተደረገ ስብሰባ የተላለፈ ውሳኔ አይጸናም።

28.5 የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔዎችን በሚሰጥበት ጊዜ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ባለሞያዎችን ሊያማክር ይችላል።

28.6 የውሳኔ ቅጂዎች በሰብሳቢው እና በማህበሩ ጸሐፊ እየተረጋገጡ መፈረም አለባቸው፡፡

## አንቀጽ ሃያ ዘጠኝ
## ዳይሬክተሮችን ስለመተካት

29.1 የዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 23.1 ድንጋጌ ቢኖርም፣ በሂሳብ ዘመኑ ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ዳይሬክተሮች በአንቀጽ 29.3. ላይ በተመለከቱት እና በማናቸውም ምክንያቶች ከቦርድ አባልነት የለቀቁ ወይም የተገለለ እንደሆነ ያሉት ዳይሬክተሮች ለቀሪው የሹመት ጊዜ የሚተኩ ሌሎች ዳይሬክተሮችን አግባብነት ባላቸው ሕጐች መሠረት መሰየም ይችላሉ፡፡

29.2 የቦርድ አባላት በማናቸውም ጊዜ ቁጥራቸው ከ50% በታች የቀነሰ እንደሆነ የቀሩት አባላት የጐደሉትን ለማሾም አባላቱ ከጐደሉበት ጊዜ ጀምሮ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ጠቅላላ ጉባዔውን መጥራት አለባቸው፤ በጐደሉት አባላት ምትክ ሹመት እስኪደረግ ድረስ የቀሩት አባላት ባንኩን ያስተዳድራሉ።

29.3 በሚከተሉት ምክንያቶች አንድ ዳይሬክተር ከቦርድ አባልነቱ ሊገለል ይችላል:-

29.3.1 ዳይሬክተሩ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ ሲከስር ወይም ዕዳውን መክፈል ሲሳነው ወይም በዕዳው ምክንያት ሲዋሀድ፣

29.3.2 የአዕምሮ ቀውስ ሲደርስበት፣

29.3.3 በወንጀል ተከሶ ሲፈረድበት፣

29.3.4 ዳይሬክተሩ እያወቀ ከባንኩ ጋር የጥቅም ግጭት የሚፈጥሩ ተግባራቶች ላይ ሲሰማራ፣

29.3.5 ዳይሬክተሩ የባንኩን ጥቅም ማስጠበቅ ወይም የባንኩን ጥቅም ለማስጠበቅ እርምጃ መውሰድ ሲሳነው፣

29.3.6 ቦርዱ በስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ እና በሥነ-ምግባር ደንብ ውስጥ በደነገገው ሌላ ምክንያት።

## አንቀጽ ሰላሳ
## አክሲዮኖችን በዋስትና ስለማስቀመጥ

30.1 ዳይሬክተሮች ኃላፊነታቸውንና ተግባራቸውን በትክክልና በሚገባ ለመወጣታቸው ዋስትና ይሆን ዘንድ እያንዳንዳቸው 25 (ሃያ አምስት) የተመዘገቡ አክሲዮኖች በባንኩ ዘንድ ማስያዝ አለባቸው፡፡ ዳይሬክተሮቹ ዳይሬክተርነታቸውን ካልለቀቁና ባንኩ በኃላፊነታቸው የሚፈለግባቸው ምንም ነገር አለመኖሩ ካልተረጋገጠ በስተቀር ዋስትናቸው አይወርድም።

30.2 ባንኩ ለቦርድ አባላቶቹ የሙያ ዋስትና ኢንሹራንስ ሊገባላቸው ይችላል።

## አንቀጽ ሰላሳ አንድ
## የዋና ስራ አስፈፃሚ እና ምክትል ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚዎች

31.1 የባንኩ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በዳይሬክተሮች ቦርድ ይሾማል፡፡

31.2 በዋና ሥራ አስፈፃሚው አቅራቢነት ቦርዱ ምክትል ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚዎች/ምክትል ፕሬዚዳንቶች ይሾማል፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ ሁለት
## የዋና ሥራ አስፈፃሚ ሥልጣንና ተግባር

32.1 አክሲዮን ማህበሩ በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሾም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ይኖረዋል፡፡ የዋና ሥራ አስፈፃሚው ተጠሪነት ለቦርድ ሆኖ፤ ደመወዙና ጥቅማ ጥቅሙም በቦርዱ ይወሰናል፡፡

32.2 የአክሲዮን ማህበሩን ጠቅላላ የዕለት ተዕለት ሥራ ይመራል፤ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት አክሲዮን ማህበሩን ይወክላል፡፡

32.3 የባንኩ ዋና ሥራ አስፈፃሚና ከፍተኛ ተጠሪ በመሆን የባንኩን አስተዳደር በበላይነት ለመምራት አጠቃላይ ሥልጣንና ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

32.4 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ዋና ሥራ አስፈፃሚው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

32.4.1 በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ የተመለከቱትን ዓላማዎች ለማሟላት በባንኩ ስም እና ባንኩን ወክሎ ይሠራል፣

32.4.2 ባንኩ በዓለም አቀፍ እና በሀገር ውስጥ በሚያካሄዳቸው ሥራዎች ምክንያት በሦስተኛ ወገኖች፣ በመንግሥታትና የግል ድርጅቶች በባንኮችና በሌሎች የገንዘብ ተቋማት ዘንድ ባንኩን ይወክላል፣

32.4.3 የአክሲዮን ማህበሩን የሥራ ዕቅድና በጀት፤ የረዥም ጊዜ ስትራቴጂና ፖሊሲዎች አዘጋጅቶ ለቦርድ ማቅረብ፤ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

32.4.4 የሥራ መመሪያ፤ ፕሮሲውጀር፤ ጋይድላይን፤ እና ሌሎች የአሰራር ሥነ-ሥርዓቶችን መቆጣጠሪያ ሠነዶች ያዘጋጃል፤ ያጸድቃል፤ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፡፡

32.4.5 የሥራ ድርሻን፤ ኃላፊነት፤ ሥልጣን፤ የሥራ ክፍፍል የሚያሳይ የአክሲዮን ማህበሩን ድርጅታዊ መዋቅር (የኦርጋናይዜሽናል ስትራክቸር) አዘጋጅቶ ለቦርድ ማቅረብ፤ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

32.4.6 የዋና ሥራ አስፈፃሚ ምክትል የሆኑ ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚዎች /ሲኒየር ኤክስኪዩቲቭ ኦፊሰሮች/ ይመርጣል፤ ለቦርድ በማቅረብ ሹመታቸውን ያጸድቃል፡፡

32.4.7 የባንኩን የሂሳብ አያያዝ በሚመለከት አመራር ይሰጣል፤ ተገቢውን ቁጥጥር ያደርጋል፣

32.4.8 የባንኩን የዕለት ተዕለት ሥራ ለማከናወን መደበኛ የማኔጅመንት ስብሰባዎችን ያደርጋል፣ በሕጉ፣ በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍና በባለአክሲዮኖች ጉባዔ በሚወሰነው መሠረት የተፈቀደለትን የመጠባበቂያ ሂሳብ እና ሌሎች የመጠባበቂያ ሂሳቦችን ያቋቁማል፤

32.4.9 በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍና በዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ መሠረት የተሰጡትን ሥልጣኖች ለባንኩ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፣

32.4.10 የባንኩን ጥቅም በመጠበቅ ከባንኩ ሠራተኞች ውጭ ጠበቃ ለማቆም ወኪሎች ለመሾም እንዲሁም ሌሎች ባለሞያዎች ለመቅጠርና ለማሰናበት ሥልጣን ይኖረዋል፣

32.4.11 ቦርዱን በቅድሚያ በማሳወቅ በባንኩ ስም በማናቸውም ባንኮች ተንቀሳቃሽ ሂሳብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፣

32.4.12 የሃዋላ ቼኮችን፣ የምንዛሪ ሠነዶችን፣ የተስፋ ሠነዶችን ሌሎች የማይተላለፉ ሠነዶችን እንዲሁም የገቢና ወጪ ንግድ ማስታወቂያዎችን ይፈርማል፣ ያጸድቃል፣ ቅናሽ ያደርጋል፣

32.4.13 ባንኩን ከኪሳራ፤ ከጥፋት፣ ከድንገተኛ አደጋና ከማናቸውም ዓይነት ዕዳ ለመጠበቅ የሚያስችል የመድን ዋስትና ከታወቀ የመድን ኩባንያ ወይም ሰው ጋር ይዋዋላል፣

32.4.14 በዳይሬክተሮች ቦርድ ቅድሚያ ፍቃድ መሠረት ከባንኩ ዓላማዎች ሳይወጣ በሥራ ላይ ያልዋለውን ገንዘብ ኢንቨስት ያደርጋል ወይም በአትራፊ ሥራ ላይ ያውላል፣

32.4.15 ዋና ሥራ አስፈፃሚው በቦርድ ከሚሰየሙት ኃላፊዎች በስተቀር በሕግ አግባብ ሠራተኛ የመቅጠር፣ የማሳደግ፣ ከደረጃ ዝቅ የማድረግና የማሰናበት ሥልጣን አለው፣

32.4.16 የባንኩን የሥራ ዕቅድ እና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርድ በማቅረብ ያጸድቃል፡፡

32.4.17 ከተያዘው ዓመት በፊት የነበረውን የባንኩን ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ የሚመለከት ዘገባ ያቀርባል፣

32.4.18 በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ ውስጥ መደረግ ስለሚያስፈልጋቸው ማናቸውም ማሻሻያዎች ለዳይሬክተሮች ቦርድ ሃሳብ ያቀርባል፣

32.4.19 ለባንኩ የዕለት ከዕለት ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ሕጋዊ ወጪዎችና ክፍያችን ይፈቅዳል፣

32.4.20 በቦርዱ ሰብሳቢ ሲጠየቅ ከማህበሩ ጸሐፊ ጋር በመተባበር የቦርዱን ረቂቅ የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፣

32.4.21 ከቦርዱ ሰብሳቢ ጋር በመመካከር እና ከማህበሩ ጸሐፊ ጋር በመተጋገዝ የቦርድ ስብሰባዎችን ዝግጅት ያስተባብራል፣

32.4.22 የብሔራዊ ባንክ መመሪያ በሚፈቅደው መሠረት ለባንኩ ጥቅም ለማስጠበቅ ተላላፊ የገንዘብ ሠነዶችን በዋስትና በማስያዝ ከብሔራዊ ባንክ መበደር ይችላል ፡፡

32.4.23 በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ ያልተጠቀሱ ነገር ግን ለአክሲዮን ማህበሩ ዓላማዎች መሳካት አስፈላጊ የሆኑትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡

32.4.24 በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሰጡትን ተግባራት የማከናወንና የቦርዱን ውሳኔዎች የማስፈፀም ኃላፊነት አለበት፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ ሦስት

## የውጭ ኦዲተሮች ስያሜ፤ ኃላፊነትና ተግባር

33.1 የባንኩ የውጭ ኦዲተሮች በባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ይሰየማሉ፡፡ ሆኖም ሹመቱ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መጽደቅ አለበት፡፡

33.2 የውጭ ኦዲተሮች ተግባርና ኃላፊነት በንግድ ሕግ፤ በባንክ ሥራ አዋጅ፤ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት ይፈፀማል፡፡

33.3 የውጭ ኦዲተሮች ስለ ሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ፣ ስለንብረት እና ዕዳ ተመን፣ መሠረታዊ የሂሳብ መርሆዎች እና አግባብነት ባላቸው ሕጐች መሠረት ኃላፊነታቸውን በጥንቃቄ ማከናወን አለባቸው፡፡

33.4 የውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት ከባንኩ የበጀት ዓመት ማብቂያ በኃላ አግባብነት ባላቸው ሕጐች ላይ በተደነገገው መሠረት ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ይሰጣል፡፡

33.5 የውጭ ኦዲተሮች የሦስት ተከታታይ ሂሳብ ዓመት ኦዲት እንዲያደርጉ በጠቅላላ ጉባዔ ሊሾሙ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ አራት

## የማህበሩ ጸሐፊ ሹመት፤ ሥልጣንና ተግባር

34.1 የማህበሩ ጸሐፊ በዋና ሥራ አስፈፃሚው አቅራቢነት በዳይሬክተሮች ቦርድ ይሾማል፡፡ የማህበሩ ጸሐፊ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

34.1.1 የባንኩን መረጃዎችና መዛግብት የማደራጀትና የመያዝ፣

34.1.2 ለሚመለከተው አካል ሪፖርቶችንና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን በወቅቱ የመስጠት፣

34.1.3 ለባለአክሲዮኖችና ለሦስተኛ ወገኖች መረጃ የመስጠት፤

34.1.4 የባለአክሲዮኖችና የቦርድ አባላትን ስብሰባዎች የማዘጋጀት፤

34.1.5 ቃለ-ጉባዔዎችን ማዘጋጀትና አደራጅቶ የመያዝ፤ እና

34.1.6 በዋና ሥራ አስፈፃሚው እና በዚህ የመመሥረቻ ጽሑፍ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት የማከናወን፡፡

# ምዕራፍ አራት

## ስለባንኩ ሂሳብ አያያዝና ተዛማጅ ተግባራት

### አንቀጽ ሰላሳ አምስት

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

35.1 አግባብነት ባላቸው ሕጐች እና በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ውስጥ ስለሂሳብና መዝገብ አያያዝ የተደነገጉት ለባንኩ ሂሳብ አያያዝና አመዘጋገብ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

### አንቀጽ ሰላሳ ስድስት

### የፋይናንስ መዝገቦችና መረጃዎች

36.1 አግባብነት ባላቸው ሕጐች መሠረት የባንኩን የሥራ እንቅስቃሴ እና ያለውን የገንዘብ አቋም በግልጽና በትክክል የሚያስረዳ መዝገቦች በአግባቡ መያዝ አለበት፡፡

36.2 ባንኩ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታች ሲያጋጥሙት ዝርዝር ጉዳዩን ወዲያውኑ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማሳወቅ አለበት፡-

36.2.1 ለገንዘብ አስቀማጮች ወይም ለሌሎች አበዳሪዎች ባንኩ ግዴታውን ለመፈፀም ያልቻለ ከሆነ፣

36.2.2 ለገንዘብ አስቀማጮች ወይም ሌሎች አበዳሪዎች የሚያደርገውን ክፍያ ለማቋረጥ የተገደደ ሲሆን፣

### አንቀጽ ሰላሳ ሰባት

### የማህበሩ የሂሳብ ዓመትና ሪፖርት

37.1 የአክሲዮን ማህበሩ የሂሳብ ዓመት እ.ኤ.አ ከሐምሌ 1 ቀን ጀምሮ በሚቀጥለው ዘመን ሰኔ 30 ያበቃል፡፡

37.2 የዳይሬክተሮች ቦርድ በእያንዳንዱ የሂሳብ ዘመን ማብቂያ ላይ ቦርዱ በዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚቀርብለትን ሪፖርት መነሻ በማድረግ የአክሲዮን ማህበሩን አጠቃላይ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፡፡

37.3 ሪፖርቱ ስለአክሲዮን ማህበሩ ትርፍና ኪሳራ እንዲሁም ስለዳይሬክተሮችና ስለኦዲተሮች ክፍያ ዝርዝር መረጃና እንዲሁም ስለመጠባበቂያ ገንዘብ ምደባና ስለዘመኑ የትርፍ ድርሻ አመዳደብ ሃሳቦችን ያቀፈ ሆኖ መገኘት አለበት፡፡

### አንቀጽ ሰላሳ ስምንት

### የሂሳብ ሠነዶችን እና ሪፖርቶችን ስለመስጠት

38.1 በንግድ ሕጉ አንቀጽ 427 መሠረት የባንኩ የንብረት ዝርዝር (Inventory)፣ የሀብት እና ዕዳ ሂሳብ መግለጫ፣ የትርፍና የኪሳራ መግለጫ እንዲሁም የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት የዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ ከመደረጉ ቢያንስ ከ40(አርባ) ቀናት አስቀድሞ ለኦዲተሮች እና ለሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች መላክ አለበት።

## አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝ
## በጥሬ ገንዘብ ስለሚያዙ ሂሳቦችና የመጠባበቂያ ገንዘብ

39.1 ባንኩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የመቶኛ ስሌት መጠን ጥሬ ገንዘብ እና ጥሬ-ገንዘብ አከል የሆኑ ሠነዶችን /ሊኩይድ አሴት/ ይይዛል፡፡

39.2 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው በሚወስነው የመቶኛ ስሌት መጠን ልክ ባንኩ በተቀማጭነት ከተቀበለው ገንዘብ ውስጥ ለመጠባበቂያ የሚሆን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንዲቀመጥ ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ አርባ
## በቸልተኝነት ወይም እምነት ማጉደል ምክንያት ለሚደርሱ ኪሣራዎች የሚሸፈኑባቸው መጠባበቂያዎች

40.1 ባንኩ በማናቸውም የወንጀል ድርጊት፣ ቸልተኝነት ወይም እምነት ማጉደል ምክንያት በባንኩ ላይ ለሚደርስ ኪሣራ መሸፈኛ የሚሆን መጠባበቂያ ገንዘብ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አስተያየት ይበቃል ተብሎ የሚታመንበትን መጠን በልዩ ሂሳብ ሊይዝ ይችላል፡፡

40.2 ከእንደዚህ ዓይነቱ ኪሣራ ራሱን ለመጠበቅ ባንኩ ተገቢ ፈቃድ ካለው ዕውቅ የኢንሹራንስ ድርጅት ዘንድ የመድን ዋስትና ሊገባ ይችላል።

## አንቀጽ አርባ አንድ
## ሌሎች የመጠባበቂያ ሂሳቦች

41.1 ባንኩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ የሚጠይቀውን በማሟላት ቀጥሎ የተመለከቱትን ወጭዎች የሚሸፍኑ የመጠባበቂያ ሂሳቦች ሊይዝ ይችላል፡-

41.1.1 የንብረት እርጅና ቅናሽ እና የተጠራቀመ የእርጅና ቅናሽ፣

41.1.2 በየዓመቱ ለተጠራቀሙ ኪሳራዎች መሸፈኛ ፣

41.1.3 ባንኩን ለማስፋፋት፣ ቅርንጫፍ ለማቋቋም፣ የንግድ መደብር ወይም የንግድ መልካም ስም /ጉድዊል/ ለመግዛት የሚደረጉትን ወጭዎች አክሲዮኖችን ለመሸጥ የሚከፈለውን ኮሚሽን ጭምር የሚሸፍኑ፣

41.1.4 በማንኛውም ውል መሠረት በመያዣነት የተያዙ ንብረቶችን ለማረጋገጥ የወጡ ወጪዎችን፡፡ ይህ የሚደረገው ግን ግዴታዎቹ ባንኩ ስለ ካፒታል እና መጠባበቂያ ገንዘብ የሚፈለጉበትን ሕጋዊ መለኪያዎች ማሟላቱን ለማረጋገጥ ሲባል ከተደረገው ስሌት ውስጥ ያልተጠቃለለ ከሆኑ እና የንብረቶቹም ዋስትና ወይም በመያዣነት መስጠት ባንኩ ሊያገኛቸው የማይችልበትን ውጤት አስከትሎበት የአስቀማጮች ዕዳዎችን እንዳይወጣ የሚያደርገው ሲሆን ነው፡፡

41.1.5 በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት ተፈላጊ ለሆኑ ጉዳዮች ወጭ የሚሆን ሌላ መጠባበቂያ ሂሳብ መያዝ አለበት፡፡

## አንቀጽ አርባ ሁለት
## የትርፍ ድርሻ አመዳደብና አከፋፈል

42.1 በንግድ ሕጉ ከአንቀጽ 432 እስከ አንቀጽ 439 የተደነገጉት እና በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 39 ላይ የተቀመጠው እንደተጠበቁ ሆኖ የትርፍ ክፍፍሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚያቀርበው ሃሳብ መሠረት፣ የባንኩ ኦዲተሮች ከመረመሩትና የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ካጸደቀው በኋላ ከተጣራው ትርፍ ላይ ታክስ፣ ሕጋዊ የመጠባበቂያ ገንዘብ፣ በባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የተፈቀዱ ሌሎች የመጠባበቂያ ገንዘቦች፣ ያለፉት ኪሳራዎች እና ሌሎች ተቀናሾች ከተቀነሱ በኃላ በአንድ ጊዜ ክፍያ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

42.2 ትርፍ ለባለአክሲዮኖች በሚከፋፈልበት ጊዜ የሚከተሉት ሁለት ነገሮች ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡-

42.2.1 ከተከፈለው ጠቅላላ ካፒታል ውስጥ እያንዳንዱ ባለአክሲዮን ያለው የተከፈለ ካፒታል መጠን፣

42.2.2 በበጀት ዓመቱ ውስጥ የአክሲዮኖች ዋጋ በሙሉ ወይም በከፊል ተከፍሎ በባንኩ እጅ የቆየበት ጊዜ ናቸው።

42.3 ከጸደቀው የሂሳብ መዝገብ ውጭ የሚደረግ ማናቸውም የትርፍ ድርሻ ክፍያ ያልተገኘ ትርፍ እንደመክፈል ስለሚቆጠር የወንጀልና የፍ/ብሔር ኃላፊነት ያስከትላል፡፡

42.4 የትርፍ ድርሻ የሚከፈልበት ቀንና ሁኔታ በባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ አርባ ሦስት
## ካፒታል በሚቀነስበት ጊዜ የሚደረግ የትርፍ ክፍፍል ዕገዳ

43.1 የባንኩ ዋና ካፒታልና መጠባበቂያ ሂሳብ ከሚገባው በታች በሚቀንስበት ጊዜ ጉድለቱን ለማስወገድ የሚቻልበት እርምጃ በብሔራዊ ባንክ ውሳኔ መሠረት ከሚደረገው የገንዘብ ማዘዋወር በስተቀር፣ በዋናው ካፒታል ላይ የታየው ቅናሽ በሕጉ በተቀመጠው መሠረት ወጭ የተደረገው ካፒታል በሙሉ እስኪተካ ድረስ ባንኩ በማናቸውም ጊዜ ትርፉን አያሳውቅም ወይም አያከፋፍልም ወይም ከትርፍ ላይ ምንም ዓይነት የገንዘብ ዝውውር አይፈፀምም፡፡

## አንቀጽ አርባ አራት
## ስለምዝገባና ሪፖርቶችን ይፋ ስለማድረግ

44.1 በዚህ የመመሥረቻ ጽሑፍ ላይ የሚደረገው ማናቸውም ማሻሻያ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ከጸደቀ በኋላ አግባብ ባለው ሕግ በተደነገገው መሠረት ይመዘገባል፡፡

44.2 አክሲዮን ማህበሩ በውጭ ኦዲተሮች የተረጋገጠ የሂሳብ ሚዛን፤ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚሰራጭ ጋዜጣ እንዲታተም ይደረጋል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ስለባንኩ መፍረስ እና ሂሳብ ስለማጣራት

### አንቀጽ አርባ አምስት

### የአክሲዮን ማህበሩን ለማፍረስ የሚያበቁ ምክንያቶች እና አግባብነት ያላቸው ሥነ-ሥርዓቶች

45.1 የአክሲዮን ማህበሩ አግባብ ባለው ሕግ በተመለከተውና በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ መሠረት ሊፈርስ ይችላል፡፡

45.2 ከሚከተሉት ምክንያቶች ውስጥ ማናቸውም ቢሆን ለአክሲዮን ማህበሩ መፍረስና ሂሳብ ማጣራት በቂ ሆኖ ይቆጠራል፡፡

45.2.1 የማህበሩ ዓላማ ተግባራዊ ሳይሆን ሲቀር ወይም ማህበሩ ተግባሩን ለማከናወን ከአቅሙ በላይ የሆኑ ምክንያቶች ሲያጋጥሙት፤

45.2.2 አክሲዮን ማህበሩ በፈቃደኝነት እንዲፈርስ በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ሲወሰን፤

45.2.3 ማናቸውም የጥቅም መብት ያለው በሚያቀርበው አቤቱታ መሠረት ፍ/ቤት አክሲዮን ማህበሩ የሚፈርስበት በቂ ምክንያት መኖሩን በማረጋገጥ እንዲፈርስ ትዕዛዝ ሲሰጥ፤

45.2.4 አክሲዮን ማህበሩ በመክሰሩ ምክንያት የዕዳ ማጣራትና የኪሳራ ፋይል በፍ/ቤት ሲከፈት፤

45.2.5 ካፒታሉ በሦስት አራተኛ ሲቀንስ፤

45.3 አክሲዮን ማህበሩ እንዲፈርስ ጠቅላላ ጉባዔው ሲወሰን ሂሳብ አጣሪዎችን ይሾማል፡፡

45.4 ማንኛውም የአክሲዮን ማህበሩ አባልም ሆነ ኦዲተር የሂሳብ አጣሪዎችን ሹመት በመቃወም ያመለከተ እንደሆነ የቀረበው መቃወሚያ በቂ ምክንያት ያለው ሆኖ ካገኙት ጠቅላላ ጉባዔው ሹመቱን ሊሽረው ወይም ሊያስቀረው ይችላል፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

## ሌሎች ድንጋጌዎች

### አንቀጽ አርባ ስድስት

### አክሲዮን ማህበሩ በሥራ የሚቆይበት ጊዜ

46.1 አክሲዮን ማህበሩ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ነው፡፡

## አንቀጽ አርባ ሰባት

## በከፊል የተሻሩ ሠነዶች

47.1 በቁጥር 359113 በ14/5/1988 ዓ.ም የተመዘገቡት የአቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማህበር መመሥረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ ሠነዶች ጋር አባሪ ተደርጎ የአቢሲንያ ባንክ መሥራች አባላት ስምና ፊርማ ዝርዝር ፀንቶ እንዲቀጠልና የዚህ የተሻሻለ የመመሥረቻ ጽሑፍ አካል ሆነው እንዲቆጠሩ ተወስኗል፡፡

47.2 ከላይ በተራ ቁ. 47.1 ፀንቶ እንዲቀጥል ከተወሰነው ውጭ ያሉ ሌሎች በቁጥር 359113 በ14/5/1988 ዓ.ም የተመዘገቡት የአቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማህበር መመሥረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ ላይ የተገለፁ ድንጋጌዎች እንዲሻሩ ተወስኗል፡፡

47.3 በተለያየ ጊዜ በተደረጉ የባለክሲዮኖች አስቸኳይ ጉባዔ ስብሰባ ቃለ-ጉባዔ የተደረጉ የቀድሞው የመመሥረቻ ጽሑፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያዎች የሚመለከተው ውሳኔዎች ብቻ ተለይተው ተሽረው በዚህ ሠነድ እንዲተኩ ተወስኗል፡፡

## አንቀጽ አርባ ስምንት

## ልዩ ልዩ ጉዳዮች

48.1 ይህ የመመሥረቻ ጽሑፍ፤ በማናቸውም ጊዜ በባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ሊሻሻል ይችላል፡፡

48.2 በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍና አግባብነት ባላቸው አስገዳጅ ሕጎች መካከል መቃረን ሲኖር አግባብነት ያላቸው ሕጎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ ውስጥ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ በንግድ ሕጉና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተደነገጉትን በመከተል ይተገበራል።

48.3 በዚህ የመመሥረቻ ጽሑፍ የአማርኛው ቅጂና የእንግሊዘኛው ቅጂ መካከል የትርጉም ልዩነት የተፈጠረ እንደሆነ የአማርኛው ቅጂ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

48.4 ይህ መመሥረቻ ጽሑፍ በባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ከጸደቀ በኋላ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ሲያገኝ እና በሚመለከተው አካል ሲመዘገብ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ኅዳር 8 ቀን 2016 ዓ.ም

------------//------------